የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የውዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

የሰ.መ.ቁጥር 241285

ቀን 30/09/2016 ዓ/ም

ዳኞች ፡- ሱልጣን አባተማም

ሽመክት አሰፋ

አብርሃ መሰለ

ተናኜ ጥላሁን

ዘውዲቱ ታደሰ

አመልካች፡- አቶ ነጃህ አብዲ ኢብራሂም ፡-

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ጀማል አረብ ኩርዬ፡-

2. አቶ መሀመድ አብዲ አሊ፡-

3. አቶ አብዱቃድር መሐመድ መሀሙድ ፡-

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

# ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ 1ኛ ተጠሪ ተከሳሽ ሲሆኑ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ደግሞ ጣልቃ ገቦች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካች ክስ ይዘት 1ኛ ተጠሪ ንብረቴ እንያስተዳድር የሰጡትን ውክልና መሰረት በማድረግ በስሜ የተመዘገበውና የግል ንብረቴ የሆነው ነጃህ ፕላዛ ህንጻ በአካል ቀርቤ ባልፈረምኩበትና ነጻ ፍቃዴ ባልሰጠሁት ሁኔታ 1ኛ ተጠሪ እርሱ ስጦታ ሰጪ እና እርሱ ስጦታ ተቀባይ ሆኖ ወደራሱ ስም ካርታ አስቀይሮ የንብረት ባለቤት የሆነው ከፍ/ብ/ህ/ቁ.2209/1/ የተጣለው ክልከላ በመጣስ ስመ-ንብረቱ በማዞር የተወሰደው ንብረቴ እንዲመልስ ተብሎ እንዲወስን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 1ኛ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርቦ የመጀመሪያ መቃወሚያና ፍሬ ነገር የሰጠው መልስ በፌዴራል ህገ መንግስት አንቀጽ 40 ስር እንዲሁም በክልሉ ህገ መንግስት መሰረት መሬት የመንግስት ነው ግንባታው ያከናወንኩት ደግሞ እኔ ነኝ፡፡ በመሆኑ ከሳሽ በእኔ ላይ ክስ ለማቅብ መብትና ጥቅም የለውም እንዲሁም ክስ የቀረበበት ንብረት በዝርዝር አልተገለጸም በማለት የቀረበው መቃወሚያ በብይን ውድቅ መደረጉ በፍሬ ጉዳይ ደግሞ ለክርክር መነሻ የሆነው መሬት መጀመሪያ ለኢንቨስትመንት የተሰጠው ለቤተሰቦችን ነበር ከዚያ የቤተሰባችን አባል የሆነው ከሳሽ ስም እንዲሆን ተደረገ እርሱ ኢንቨስት ለማድረግ ሳይችል በመቅረቱ እኔ ኢንቨስት አድርግበታለሁ ብየው እርሱም ፈቅዶልኝ መሬቱን የሰጠን መንግስት 4000 ካ/ሜ ተመላሽ ተደርጎ

ለሌሎች ሁለት ሰዎች አከፋፍሎ ቀሪው 5000 ካ/ሜ ላይ ሌሎች ሁለት ሰዎች በህብረት ኢንቨስትመንት አከናውንበታል መሬቱ ለይ ግንበታ አልነበረውም፤



ኢንቨስት ሳደርግ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 መሰረት ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልቀረበበኝም፤ ከሳሽ በቋሚነት ሀገር ውስጥ የነበረ በመሆኑ ውጭ ሀገር ነበርኩ ያለው ተቀባይነት የለውም፤ለእኔና ለሁለቱ ሰዎች ኢንቨስት እንዲናደርግ ሙሉ ውክልና ሰጥቶን ዛሬ በሌላ አቅራረብ መቅረቡ ተገቢ አይደለም። በመሆኑም በእኔ ላይ ክስ ያቀረበበትን ድርጊት ያከናወንኩት በራሱ ፈቃደኝነት መሆኑ እና እርሱም ባለመቃወሙ ወይም ተቃውሞ ባለማቅረቡ በፍ/ብ/ህ/ቁ.1179 መሰረት  ይህ መሬት እንዲወሰንልኝ እንዲሁም በከሳሽ የቀረበው ክስ የህግ መሰረት ያለው ባለመሆኑ የክስ መዝገቡ እንዲዘጋልኝ በማለት የመከላከያ መልሱን በማቅረብ ተከራክረዋል። የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው ያቀረቡት ክርክር ከሳሽና ተከሳሽ መካከል ከነጃህ ህንፃ ፊትለፊት በሚገኘው ብሉ ሞል ህንጻ ንብረት እያንዳንዳችን 17 % ድርሻ /ሼር/ ያለን በመሆኑ ያለን ድርሻ መብት እንዲጠበቅልን ወይም ተመላሽ እንዲደረግልን በማለት አቤቱታቸውን አቅርበዋል።

በክርክሩ ሂደት ጉዳያቸውን በሽምግልና ለመጨረሽ ለፍርድ ቤቱ ባቀረቡት መሰረት ስምምነት በማድረግ ከተፈረመ በኂላ በጠቅላይ አቃቤ ህግና ፍትህ ቢሮ የጸደቀ ስምምነት ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል። በስምምነቱ መሰረት ድርሻቸው የአሁን አመልካች ከነጃህ ብሉ ሆቴል/ብሉ ሞል/39% ፤የአሁን 1ኛ ተጠሪ  27% ፤ የአሁን 2ኛ ተጠሪ 19% እና የአሁን 3ኛ ተጠሪ 39% መሆኑን በመግለጽ ለከሳሽና ተከሳሽ የተሰጠ ካርታ ተመላሽ ተደርጎ ካርታው ለሁለት እንዲካፈል፤ብሉ ሆቴል የተገነባበት 5000 ካ/ሜ ለሁለት ተከፍሎ 2800 ካ/ሜ በብሉ ሆቴል እንዲዘጋጅ ፤ቀሪው 2000 ካ/ሜ ደግሞ ካርታ በሐላል ሱፐር ማርኬት ድርጅት ስም እንዲዘጋጅ፤በፍ/ብ/ስ/ስስ/ቁ.274 እና 275 እንዲሁም በፍ/ብ/ህ/ቁ.3307 -3324 ድንጋጌ መሰረት ወስኗል። በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች የይግባኝ አቤቱታውን ለሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ በማጽናት ወስኗል። በመቀጠል አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቀርበዋል። ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ክርክር ከሰማ በኂላ  የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት በውሳኔ በማጽናት ወስነዋል።

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሶማሌ ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች ጥር 24 ቀን 2015 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የሰበር አመልካች ክሴን አቋርጫለሁ ባሉበት በግልግል ጉባኤ ጉዳዩ እንዲወሰን አልተስማማሁም ባሉበት እና ግልጽ የግልግል ዳኝነነት ውሳኔ ባልቀረበበት በግልግል ዳኝነት ያለቀ ነው፤ብለው በየደረጃው ያሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች የወሰኑበት አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት የ1ኛ እና 3ኛ  ተጠሪዎች ጠበቃ በሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ መልስ እንዲሁም የ2ኛ ተጠሪ ጠበቃ ደግሞ በነሐሴ 02 ቀን 2015 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም ተጠሪዎች በሰጡት መልስ ላይ አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱ፡- 1ኛ ተጠሪ አመልካች በውጭ ሀገር ስለምኖር የሰጠሁትን ውክልና በመጠቀም የሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ የስራ ሂደት ሰራተኞች ጋር በመመሳጠር የጥቅም ግጭት ያለበትን ሕገወጥ እና ሀሰተኛ የስጦታ ሰነድ በማፀደቅ፣ ይህንኑ ሰነድ ተጠቅሞ እና የጅግጅጋ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ሰራተኞችን በማጭበርበር በስሜ ካርታ የወጣበትንና ተመዝግቦ የነበረውን ነጻህ ፕላዛ ህንጻን ወደ ራሱ ስም አዛውሯል፤ በካርታ ቁጥር 8986/12 ካርታውን በስሙ አስቀይሮ የንብረቱ ባለቤት ሆኗል፤ በዚህ የተነሳ ከሕግ አግባብ ውጭ 1ኛ ተጠሪ እራሱ ስጦታ ሰጪን ወክሎ እና እራሱ ስጦታ ተቀባይ ሆኖ በፈረመው የስጦታ ውል አማካኝነት ስመ-ሀብቱን በማዞር የተወሰደው ንብረቴ ይመለስልኝ በማለት በሶማሌ ክልል ፋፋን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ አቅርቤያለው፤ በዚህ ጊዜ ፍ/ቤቱ ጣልቃ ገቦችን ጣልቃ አስገብቶ ግራቀኛችን እያከራከረ እያለ የአካባቢው ሽማግሌዎች እኛን ለማስማማት ወደ ጉዳዩ በመግባታቸው የተነሳ በጉዳዩ ላይ በመረጥናቸው ሽማግሌዎች ተስማምተን እንድንቀርብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቷል፤ በዚህ መሰረት በመረጥናቸው ሽማግሌዎች ለመስማማት የተቀመጥን ቢሆንም ስምምነት ላይ ልንደርስ ባለመቻላችን ተጠሪዎች በክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን እንድታሰር በማድረግ ጫና ሲያደርጉብኝ ቆይተዋል፤ ለክሴ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በሚመለከተው የመንግስት አካል ምላሽ ያገኘ በመሆኑ ክሴን በማቋረጥ የክስ መዝገብ አዘግቼ እያለሁ ተጠሪዎች አመልካች በችሎት ሳልቀርብ ሳላስከፍት የተዘጋው መዝገብ በራሳቸው እንዲንቀሳቀስ ካደረጉ በኋላ ፍርድ ቤቱ ስምምነቱን ተቀብሎ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ መሰጠቱን ከወራት በኋላ ከእስር ስፈታ አውቄያለሁ፤የስር ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ከሥነስርዓት ውጪ በአመልካች የተቋረጠን ክስ በእራሱ አንቀሳቅሶ ውሳኔ መስጠቱ ከሕግ ውጪ ነው፤ የሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ይግባኙ የቀረበው በግልግል ስምምነት ላይ ነው፣ በግልግል ስምምነት ላይ ይግባኝ እንደማይባል ሕጉ ይከለክላል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ማፅናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሻር ይገባል የሚል ሲሆን 1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በበኩላቸው አከራካሪው ሕንጻ የተሰራበት ይዞታ በ5000 ካ.ሜ ቦታ ላይ ሲሆን አመልካች አቤቱታ ያቀረቡት በ9000 ካ.ሜ ላይ በመሆኑ ፍ/ቤቱን የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲወስድ የተደረገ ነው፤1ኛ ተጠሪ የአመልካች ወንድም በመሆኔ ይዞታችን እንዳይወሰድ የሌሎች ተጠሪዎችን ገንዘብ ጨምሬ ሕንጻዎቹን ገንብቻለሁ፤ በስር ፍ/ቤት በተደረገ ክርክርም ሕንጻዎቹን የገነባሁት 1ኛ ተጠሪ መሆኔን አመልካች አምኗል፤ተጠሪዎች ይዞታው ላይ የተገነባው ንብረት ላይ ያለን ድርሻ ተለይቶ በስምምነት በውልና ማስረጃ ፀድቋል፤ አመልካች በሽማግሌዎች ፊት የተደረገው ስምምነት ላይ ያለማንም አስገዳጅነት በሙሉ ፈቃድና ፍላጎት ፈርሟል፤ እንዲሁም በመመስረቻና መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በሶማሌ ክልል ጅግጂጋ ቅርንጫፍ ባለው ውልና ማስረጃ ቀርቦ ፈርሟል፤ ይህንም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ ከሆነ በፎረንሲክ ምርመራ ማረጋገጥ ይችላል፤ አመልካች ችሎት ላይ ቀጠሮ በነበረው ጊዜ ሁሉ ከጠበቃው ጋር ይቀርብ ነበር፤ ስምምነቱም የጸደቀ ጊዜ ችሎት ቀርቦ ስምምነቱ እንዲጸድቅ ተስማምቷል፤ አመልካች እስር ላይ ነበርኩ ያለውን በተመለከተ ለተወሰኑ ቀናት በግል ጉዳዩ ታስሮ የነበረ ቢሆንም ጊዜው ከሽምግልናውም ጊዜም ሆነ ፍ/ቤቱ ስምምነቱን ካጸደቀበት ጊዜ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም፡፡ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካች ከፍተኛ ፍ/ቤት ክሴን በራሴ ጊዜ አቋርጬ እያለው መዝገቡ ተንቀሳቀሶ ውሳኔ መሰጠቱ አግባብ እይደለም በማለት የገለጹትን በተመለከተ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካችና 1ኛ ተጠሪ መካከል በነበረዉ የፍትሐ ብሔር ክርክር 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መብትና ጥቅም ያላቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ገብተዉ እንዲከራከሩ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
የውዝፍ መዛግብት ሰበር ችሎት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸምዓለማእ የገ ለግልም!

ተፈቅዶላቸቸዉ ጉዳዩን በእርቅ እንድንጨርሰዉ ከሁላችንም በኩል በቀረበ ሀሳብ አመልካች በመረጣቸዉ የጎሳ ሽማግሌዎች በተደረገ ሽምግልና በስሙ በተመዘገበዉ ይዞታ ላይ ሕንጻ የተገነባዉ በተጠሪዎች መሆኑ ተረጋግጦ በንብረቱ ላይ እንዳደረግነዉ አስተዋፅጾ በ2800 ካሬ ሜትር ይዞታዉ ላይ በተገነባዉ ንብረት ላይ ያለን ድርሻ በመቶኛ ተቀምጦ ስምምነቱ በዉልና ማስረጃ ጽ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በዉልና ማስረጃ የተረጋገጠዉና የተመዘገበዉ ስምምነት ፍርድ ቤት ቀርቦ ጸድቋል፡፡ ሌለው አመልካች በሽማግሌ ፊት የተደረግን ስምምነት በተመለከተ የተስማማን ቢሆንም አመልካችን መብት የሚጎዳ በመሆኑ ሳልስማማ ቀርቻለሁ ያለውን በተመለከተ ፈጽሞ ከእውነት ራቀ ነው፡፡፡ አመልካች በሽማግሌዎች ፊት የተደረገው ስምምነት ላይ ያለማንም አስገዳጅነት በሙሉ ፈቃድ ፍላጎት ስምምነት አድርገን ስምምነቱ ላይ ፈርሟል፡፡ ከዚህም በኋላ ሽማግሌዎቹ በሰጡት ውሳኔ ተስማምቶ ፈርሟል፡፡ እንዲሁም በመመስረቻና መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በሶማሌ ክልል ጅግጂጋ ቅርንጫፍ ባለው ውልና ማስረጃ ቀርቦ ፈርሟል፡፡ አመልካች ሌላው ስምምነቱ ፍ/ቤት ቀርቦ ሲጸድቅ እኔም ሆንኩ ተበቃዬ አልነበርንም ሚለውን በተመለከተ አመልካች ችሎት ላይ ቀጠሮ በነበረው ጊዜ ሁሉ ከጠበቃው ጋር ይቀርብ ነበር፤ ስምምነቱም የጸደቀ ጊዜ ችሎት ቀርቦ ስምምነቱ እንዲጸድቅ ተስማምቷል፡፡ በተጨማሪም እስር ላይ ነበርኩ ያለውን በተመለከተ ለተወሰኑ ቀናት በግል ጉዳዩ ታስሮ የነበረ ቢሆንም ጊዜው ከሽምግልናውም ጊዜ ሆነ ከፍ/ቤቱ ስምምነቱን ካጸደቀው ጊዜ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት የለውም፡፡ ስለሆነም አመልካች የስምምነት ሰነዱ ላይ አምነውና ፈቅደው ፈርመው ፍ/ቤት ቀርበው አጸድቀው ሲያበቁ ስምምነቱ የሽማግሌዎች ውሳኔ ነው እንጂ የግራ ቀኞችን አይደለም በማለት ግለጽ የሆነ ክህደት በመፈጸም አምነውበት በሽማግሌ እና ምስክር ፊት የፈረሙትን ስምምነት በመካድ ይህንን ፍ/ቤት ለማሳሳት በማሰብ ያቀረቡት አቤቱታ ስለሆነ አቤቱታው ውድቅ ሊደርግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንደመረመርነው የዚህ ችሎት ምላሽ የሚያሻው ጉዳይና መሰረታዊ ጭብጥም ጉዳዩ በስምምነት አልቋል መባሉ በአግባቡ ነው ወይ የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩበት ጉዳይ የአካባቢው ሽማግሌዎች ግራ ቀኞችንን ለማስማማት ወደ ጉዳዩ በመግባታቸው የተነሳ በጉዳዩ ላይ በመረጥናቸው ሽማግሌዎች ተስማምተን እንድንቀርብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ሰጥቶ በዚህ መሰረት በመረጥናቸው ሽማግሌዎች ለመስማማት የተቀመጥን ቢሆንም ስምምነት ላይ ልንደርስ  አልቻልንም፤ ስምምነቱ ላይ አልፈረምኩም፡፡ በዚህ ሁኔታ ስምምነቱ ፍ/ቤት ቀርቦ መጽደቁ ስህተት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ አመልካች በስምምነቱ ላይ ፈርመዋል ስምምነቱ የጸና ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ክርክር ባደረጉበት ወቅት ግራቀኙ ክርክራቸውን በስምምነት/በሽምግልና ለመጨረስ መስማማተቸውን አመልካችም ሆኑ ተጠሪዎች አልካዱም፡፡ አሁን አመልካች እያሉ ያሉት ለሽምግልና ተቀምጠን መስማማት አልቻልንም  ስምምነቱ ተቀባይነት ማግኘት የለበትም ብለው ነው፡፡ በመ/ቁ. 052-275-2012 በ18/02/2014 ዓ/ም የስር የሶማሌ ክልል የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ግራቀኙ የተከራከሩበት መዝገብ እንደሚያስረዳው ፍርድ ቤቱ መደበኛውን ስነስርዓት ተከትሎ ግራቀኙን እያከራከረ እያለ  ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ እንደሚገኝ በችሎት ግራቀኞቸው ቀርበው ስምምነታቸውን ለማቅረብ እንዲችሉ ተለዋጭ ቀጠሮ የጠየቁ መሆኑን እና ችሎቱም ስምምነታቸውን እንዲያቀርቡ በ01/05/2013 ዓ/ም ተለዋጭ ቀጠሮ  የያዘላቸው ቢሆንም በዚህ ቀን ሳይቀርቡ ቀርተው በ28/11/2013 ዓ/ም  ችሎት ቀርበው ስምምነታቸው እንዲጸድቅላቸው ተከራካሪ ወገኖች ቀርበው መጠየቃቸውን መዝገቡ ያስረዳል፤ ስምምነቱን ፍርድ ቤቱ  ሲገልጸው ‹‹ በግራቀኙና በክሱ ተሳታፊ ባልሆኑ ሌሎች



ወገኖች መካከል የሚገኙ የብዙ ንብረቶችን ጉዳይ መፍትሔ የተደረገበት ሲሆን ፍርድ ቤቱ በስምምነቱ ውስጥ ከቀረቡት ጉዳዮች መካከል ከቀረበለት ክስ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ወስዷል ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸውን ነጥቦች እና የስምምነት ሰነዱ እንደሚከተለው ቀርቧል›› ሲል ፍ/ቤቱ ከገለጸ በኋላ  ተከራካሪ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አይገለገልም!

ወገኖች ጉዳያቸው ለሽምጋይ እንዲቀርብ የተስማሙ መሆኑን እና በሽማግሌዎች የተወሰነውን ውሳኔ የሚቀበሉ መሆናቸውን ፈርመው ያረጋገጡበትን ሰነድ የተቀበለ መሆኑን በመዝገቡ ላይ አስፍሯል፡፡ የስምምነቱ ሰነድ በክልሉ ጠቅላይ አቃቤ ህግና ፍትህ ቢሮ ጭምር ቀርቦ የጸደቀ እንደሆነ ከመዝገቡ መመልከት ይቻላል፡፡

ከሽምግልና ኮሚቴው ውሳኔ ጋር አብሮ ብሉ ናይል በሚል ስያሜ ያቋቋሙት ድርጅት የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደርያ ደንብ ጭምር መቅረቡን ፍ/ቤቱ በመዝገቡ ላይ በግልጽ አስፍሯል፤ እንግዲህ አመልካች በስር ፍ/ቤት መዝገብ መሰረት በስምምነቱ፣ መተዳደርያ ደንቡና በመመስረቻ ጽሁፉ ሰነዶችን ለማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረጉ በመሆኑ እና የአመልካችንም ፊርማ ሳይመለከት ሰነዶችን የሚያረጋግጠው አካል እነዚህን ሰነዶች ሊመዘግብ እንደማይችልና መረዳት ይቻላል፡፡ የስምምነት ሰነዱ፣መተዳደርያ ደንቡ እና የመመስረቻ ጽሁፉ በውልና ማስረጃ የተደረጉ ከሆነ ሰነድ መዝጋቢው አካል የስምምነቱ አካላት በሰነዶቹ ላይ መፈረማቸውን እንደሚያረጋግጥ ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህም የሚመለከታቸው አካላት በሰነዱ ላይ መፈረማች የግድ እንደሆነ ያስረዳል፤ አመልካች በአንድ በኩል በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ባደረጉት ክርክር በስምምነቱ ላይ የፈረምኩት በእስር ቤት በነበርኩበት ወቅት እንደ ቅድመ ሁኔታ በመቀመጡ ተገድጄ ነው የፈረምኩት ይላሉ፡፡ ይህም ሆኖ በዚህ ችሎት ተገደው ስምምነቱን ስለመፈረማቸው በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻሉ መሆኑን ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በሶማሌ ክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ ባደረጉት ክርክር ሰምምነቱ የአንድ ወገን ስምምነት ነው በስምምነቱ ላይ ፈቃደኛነቴን አልገለጽኩም ያሉ ሲሆን በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ላይ ባቀረቡት መከራከርያም በስምምነቱ ላይ **አልፈረምኩም ስምምነቱ ሀሰተኛ ስምምነት ነው ብለው ይከራከራሉ**፡፡ ይህም አመልካች ክርክርቸውን በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ላይ እየቀያየሩ አንድ ጊዜ ተገድጄ ነው የፈረምኩት ሌላ ጊዜ ደግሞ ስምምነቱ ላይ አልፈረምኩም ክሱ እንዲቋረጥ አድርጌለሁ በማለት ወጥነት ያለው ክርክር ካልመሆኑም በላይ በማስረጃ የተደገፈ አለመሆኑን ከክርክሩ ሂደትና ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ግልባጭ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ከዚህ አንጻር ያነሱት መከራከርያ ተቀባይነት ያለው ሁኖ አልተገኘም ፡፡

አመልካች ሌላው የሚያነሱት ጉዳይም በአስተዳደራዊ መንገድ ችግሩ እንዲፈታ አድርጌ መዝገቡን ካስዘጋሁ በኋላ በችሎት ሳልቀርብ እና ራሴ ያስዘጋሁትን የተዘጋውን መዝገብ ሳላስከፍት የተዘጋው መዝገብ በራሳቸው እንዲንቀሳቀስ ካደረጉ በኋላ አመልካች ያልተስማማሁበት እና ያልፈረምኩበት ሀሰተኛ የስምምነት ሰነድ አዘጋጅተው እንዲያጸድቅላቸው በማቅረብ ከአመልካች ጋር የነበራቸውን የፍርድ ቤት ክርክር በስምምነት ለመጨረስ የተስማማን አስመስለው አቅርበው በፍርድ ቤቱ መጽደቁ ስህተት ነው ብለው ነው ፤ይሁን እንጂ ይህ መከራከርያ የስር የሶማሌ ክልላዊ መንግስት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን እውነታ የሚያስረዳ ባለመሆኑና መዝገቡ የተዘጋው በስምምነቱ ምክንያት መሆኑን መዝገቡ ስለሚያስረዳ አመልካች በዚህ ረገድ ያነሱት ጉዳይ ተቀባይነት የለውም፡፡ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች ውስጥም ይህ እውነታ ያልተገኘ በመሆኑና አመልካች በስር ያላነሱትን መከራከርያ በዚህ ችሎት ሊያቀርቡ ስለማይችሉ አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡



በአጠቃላይ ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የስር ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይምለግንዛቤ እንጂ
ለፍርዮ አረጸጸ ምዓለማአ የገለግልም!

1. በሶማሌ ክልላዊ መንግስት የፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 052-275-2012 በ18/02/2014 ዓ/ም ተሰጥቶ በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 05-1-69/14 በ10/06/2015 ዓ/ም ፤በሶማሌ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 05-1-239/14 በ07/03/2015 ዓ/ም በዋለው ችሎት በውሳኔ የጸናው ውሳኔ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር *ሥነ-ሥርዓት መመሪያ* ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሠረት ጸንቷል፡፡
2. ከዚህ ችሎት ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ውጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ

**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡**

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አይገለግልም!